

# የኖህ ታሪክ

* ኖህ እግዚአብሔርን የሚታዘዝ መልካም ሰው ነበር። እርሱ በነበረበት ዘመን የነበሩ ሌሌች ሰዎች ግን ክፉዎች ነበሩ።

* እግዚአብሔር ኖህን የጥፋት ውኃ ልኮ ምድርን እንደሚያጠፋት ነገረው።
ስለዚህ ትልቅ መርከብ እንዲሰራ አዘዘው።

* እግዚአብሔር ከሁሉም የእንስሳትና የአእዋፍ አይነቶች ሁለት ሁለት አድርጎ ወደኖህ ላካቸው። ኖህም ወደመርከቡ አስገባቸው። አንዳንድ የእንስሳት ዝርያዎች ከሁለት በላይ ሆነው ወደ ኖህ መርከብ ገቡ። ኖህ በተጨማሪም ሶስት ልጆቹና ሶስት ሚስቶቻቸውን እንዲሁም የራሱን ሚስት ይዞ መርከብ ውስጥ ገባ። ዝናብ መዝነብም ጀመረ። እግዚአብሔርም የመርከቡን በር ከውጭ በኩል ዘጋው።

* ዝናቡም ያለማቋረጥ ለ40 ቀንና ለ40 ሌሊት ዘነበ። በምድር ላይ የነበሩ ማናቸውም ነገር ከውኃ በታች ሆኑ። በምድር የቀሩ ሰዎች በሙሉ ሞቱ። ኖህና ቤተሰቡ ግን ከጥፋት ውኃ አመለጡ።

* ዝናቡ ካቆመ በኋላና ምድሩ ከደረቀ በኋላ እግዚአብሔር ቀስተደመናን በሰማይ ላይ በማድረግ ዳግመኛ ምድርን በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋት ቃል ኪዳን አደረገ።

የኖህና የጥፋት ውኃ ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት መፅሐፍ በምዕራፍ 6፣7፣8 እና 9 ከቁጥር 1 – 17 ነው።

http://gardenofpraise.com